# የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና የግል መረጃ ጥበቃ ህግ (FERPA)

# መብቶች እና የግል መለያ መረጃዎች እንዳይሰጥ መጠያቅያ ቅፅ አመታዊ ማስታወቂያ

2024-2025 አማርኛ፣ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና የግል መረጃ ጥበቃ ህግ (FERPA)** (20 U.S.C. § 1232g; 34 CFR Part 99) የተማሪ የትምህርት መዝገቦችን ግላዊነት የሚጠብቅ የፌዴራል ህግ ነው።

ስለዚህ ሰነድ ለጥያቄዎች እና ለበለጠ መረጃ፣እባክዎን ይህንን የመገናኛ ቅጽ ይጠቀሙ:
https://www.seattleschools.org/ferpa-questions/

ስለ FERPA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት:
https://studentprivacy.ed.gov/audience/parents-and-students ይጎብኙ ።

# የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል መረጃ ጥበቃ ህግ (FERPA) መብቶች ማስታወቂያ

**በ FERPA መሰረት፣ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲሁም ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸው ተማሪዎች ("ብቁ የሆኑ ተማሪዎች") የተማሪ ትምህርት መዝገቦችን በተመለከተ የተወሰኑ መብቶች አሏቸው።ተማሪው 18 አመት ከሆነ፣ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር አብሮ ቢኖርም፣ተማሪው በዚህ ህግ መሰረት ሁሉም መብቶች አሉት።እነዚህ መብቶች:**

1. ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መረጃዎችን እንዲሰጥ የጽሁፍ ጥያቄ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በ45 ቀናት ውስጥ የትምህርት መዝገቦቻቸውን የማየት እና የመገምገም መብት።

   የልጃቸውን የትምህርት መዛግብት ለማየት የሚፈልጉ ወላጆች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ለማየት የሚፈልጓቸውን መዛግብት የሚገልጽ የጽሁፍ ጥያቄ ለት/ቤቱ ርእሰመምህር ማቅረብ አለባቸው።የትምህርት ቤቱ ባለስልጣን መዝገቦችን አዘጋጅቶ የሚያዩበትን ጊዜ እና ቦታ ለወላጅ ወይም ብቁ ለሆነ ተማሪ ያሳውቃል።

2. ወላጅ ወይም ብቁ የሆነ ተማሪ መዝገቡ ትክክል አይደለም፣የተሳሳተ ነው ወይም በ FERPA መሰረት የተማሪውን የግላዊነት መብት የሚጥስ ነው ብሎ ያመነበትን የትምህርት ሪከርድ እንዲሻሻል የመጠየቅ መብት።ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መዝገቡን ላለማሻሻል ከወሰነ፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውሳኔውን ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ለሆነ ተማሪ ያሳውቃል እና የማሻሻያ ጥያቄውን በተመለከተ ይግባይ የማለት መብት እንዳላቸው ይመክራል።የይግባኝ መብትን ሂደትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ለሆነ ተማሪ ይሰጣል።

3. FERPA ያለፈቃድ ይፋ እንዲደረግ ከሚፈቅደው በስተቀር ትምህርት ቤቱ በተማሪው የትምህርት መዛግብት ውስጥ ያሉትን የግል መለያ መረጃን ይፋ ከመሆኑ በፊት የጽሁፍ ፍቃድ የመስጠት መብት።ያለፈቃድ ይፋ ማድረግን ከሚፈቅደው በተለየ ሁኔታ ህጋዊ ትምህርታዊ ፍላጎቶች ላላቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች ይፋ ማድረግ ነው።

   የትምህርት ቤት ሰራተኞች ማለት በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተቀጠሩ እንደ አስተዳዳሪ፣ተቆጣጣሪ፣ አስተማሪ ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ (የጤና ወይም የህክምና ሰራተኛ እና የህግ አስከባሪ ክፍል ሰራተኛ ጨምሮ)፣እጩ መምህር፤በትምህርት ቤት ቦርድ ውስጥ የሚያገለግል ሰው፤የሥራ ኮንትራክተሮች (እንደ ጠበቃ፣ ኦዲተር፣የሕክምና አማካሪ ወይም ቴራፒስት ያሉ ልዩ ሥራን ለማከናወን በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውል የፈፀመ ሰው ወይም ኩባንያ)፤አማካሪዎች፤በጎ ፈቃደኞች፤ወይም በኦፊሴላዊ ኮሚቴ ውስጥ የሚያገለግል ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ባለስልጣን ስራዉን፣ስራዋን፣ወይም ስራቸውን ሲያከናውኑ የሚያግዝ ወላጅ ወይም ተማሪ ማለት ነው።

   የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የትምህርት ሪከርድን ማየት ካለባቸው የትምህርት ሪከርዱን ለማየት ህጋዊ እውቅና አላቸው።

   ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ኣንድ ተማሪ ሊመዘገብበት የፈለገው ወይም የተመዘገበበት የሌላ ትምህርት ቤት ባለስልጣናት የተማሪው የትምህርት መረጃ ሲጠየቅ ካለ ፍቃድ ይሰጣል።

4. ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የFERPA መስፈርቶችን ካላሟላ ለዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት ቅሬታ የማቅረብ መብት።ቅሬታዎች በጽሑፍ በቀጥታ ወደ Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Avenue S.W.; Washington, DC 20202 መቅረብ አለባቸው።

## ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (SPS)-የግል መረጃ ማስታወቂያ

በዚህ ቅጽ ላይ በተዘረዘሩት ሂደቶች መሰረት ለሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መረጃውን እንዲለቀቅ እንደማይፈልጉ በጽሁፍ ካላሳወቁ በስተቀር፣በFERPA መሰረት፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች በ “directory information”በትክክል የተገለፁ መረጃዎች ያለ የጽሁፍ ፍቃድ ለማንም ማለትም፣ለየወላጅ-መምህር ድርጅቶች፣ለመገናኛ ብዙሃን፣ለኮሌጆች እና ለዩኒቨርሲቲዎች፣ለመከላከያ፣ለየወጣቶች ቡድኖች እና ለየስኮላርሺፕ ድጋፍ ሰጮዎችን ጨምሮ  ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ለልሎችም ሊለቅ ይችላል።

**የሚከተሉትን መረጃዎች እንደ የግል መለያ መረጃ (directory information) ይቆጠራሉ:**
የወላጅ/አሳዳጊ እና የተማሪ ስም፣የቤት አድራሻ፣የቤት ስልክ ቁጥር፣የቤት ኢሜል አድራሻ፣የተማሪ ፎቶግራፍ ወይም ቪዲዮ፣የተማሪ የትውልድ ቀን፣የተመዘገቡበት ቀን፣የክፍል ደረጃ፣የምዝገባ ሁኔታ፣የተቀበሉት ዲግሪ ወይም ሽልማት፣ዋና የጥናት መስክ፣በይፋ በሚታወቁ እንቅስቃሴዎች እና የስፖርት ቡድኖች ተሳትፎ፣የአትሌቶች ቁመት እና ክብደት፣የቅርብ ጊዜ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም፣እንዲሁም ይፋ ከሆኑ ግላዊነትን የማይጥሱ ሌሎች መረጃዎች።

**ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል (9-12) ላሉ ተማሪዎች የግል መረጃ መለቀቅን በተመለከተ መረጃ**
እርስዎ እንደ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ (18 ዓመት የደረሰ) እንደመሆኖ፣ የተማሪዎ (ወይም የእርስዎ) የግል መረጃ ስለ መልቀቅ እና ኣለ መልቀቅ  በተመለከተ ከሶስቱ(3) አማራጮች መካከል የመምረጥ መብት አሎት።(ያሉትን አማራጮች ለማየት ወደ ቀጣዩ ገጽ ይሂዱ)

**ከወታደራዊ ክፍል የሚቀርብ የግል መለያ መረጃ ጥያቄዎች**
ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ ተማሪ ምርጫ B ወይም ምርጫ C በመምረጥ የተማሪውን የግል መለያ መረጃዎች ለወታደር ክፍል ለመልቀቅ ካልከለከለ በስተቀር፣በፌዴራል ሕግ መሠረት፣የዩናይትድ ስቴትስ ወታደራዊ መልማዮች፣ “የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን” ስም፣ስልክ ቁጥሮች እና አድራሻዎች ሲጠይቁ፣የማግኘት መብት አላቸው።ወታደራዊ ክፍሉ በየጊዜው በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት በጥቅምት ወር ላይ ይህን መረጃ ይጠይቃል።መረጃ ለወታደራዊ ክፍል እንዲሰጥ ካልፈለጉ፣ምርጫዎ በጊዜ መመዝገቡን ለማረጋገጥ ምርጫ B ወይም ምርጫ C በመምረጥ እስከ **ጥቅምት 1** ድረስ ይህን ቅጽ መመለስ **አለብዎት።**

ምንም እንኳን ምርጫ B ወይም ምርጫ C መምረጥ ማለት ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መረጃ ለወታደራዊ ክፍል አይለቅም ማለት ቢሆንም፣የወታደር ክፍሉ የተማሪዎችን መረጃ ከሌሎች የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ምንጮች ሊሰበስብ ይችላል።በተጨማሪም፣ምርጫ B ወይም ምርጫ C መምረጥ ቀጣሪው በግቢው ውስጥ እያለ ወታደራዊ መልማዮች ከተማሪዎ ጋር እንዳይነጋገሩ አያግዳቸውም።እባኮትን በሚቀጥለው ገጽ አንድ አማራጭ ይምረጡ እና ይህንን ቅጽ እስከ ጥቅምት 1 ድረስ ተማሪዎ ወደሚማርበት ትምህርት ቤት ይመልሱ።

**ለየመንግስት ትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ (OSPI) ፅህፈት ቤት የሚሰጥ የግል መለያ መረጃ**

ይህንን ለመወሰን ብቁ የሆነ ተማሪ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ የግል መለያ መረጃዎችን እንዳይተላለፍ በየFERPA ቅፅ በኩል ካልጠየቁ በስተቀር፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የግል መለያ  መረጃን እስከ ህዳር 1 ቀን ድረስ ለየመንግስት ትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSPI) ያስተላልፋል።በተጨማሪም OSPI ይህንን መረጃ በRCW 28A.150.515 እና RCW 28B.10.041 መሰረት ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲተላለፍ ያደርጋል።

**ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ ከሚከተሉት አንዱ ከመረጡ፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ምርጫ A እንደተመረጠ ያስባል:**

1. ቅጹን ማቅረብ፣ነገር ግን ከሣጥኖቹ ውስጥ በአንዱ ላይ ምልክት አለማድረግ ወይም
2. ቅጹን አለመመለስ ወይም
3. አማራጭ A ከሌሎች አማራጮች በተጨማሪ ከተመረጠ

ማሳሰብያ፣ዲስትሪክቱ ተማሪዎች ለህዝብ ክፍት በሆኑ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች ላይ ሲሳተፉ ከዲስትሪክቱ ውጭ በሆኑ ምንጮች የተነሱትን ፎቶግራፎች/ምስሎች ወይም ስሞች ስርጭት መቆጣጠር አይችልም።<<<< ለምርጫ እና ለፊርማ ወደሚቀጥለው ገፅ ይሂዱ >>>> በሚያዚያ 2024 የተሻሻለ

# የFERPA የግል ማንነት መለያ መረጃዎችን ለሌላ እንዳይተላለፍ የመጠየቂያ ቅፅ(OPT-OUT FORM)- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**እባኮትን ይህን ቅጽ ሙሉ በሙሉ ሞልተው እስከ ጥቅምት 1 ድረስ ወደ ተማሪው ትምህርት ቤት ይመልሱት።**ከአንድ በላይ ተማሪዎች ካሉዎት ለእያንዳንዱ ተማሪ የተለያየ ቅጽ ይሙሉ።

ቅጾች በአካል ወይም በዩኤስ ፖስታ ሊመለሱ ይችላሉ።

**የተማሪውን** ሙሉ ስም ይፃፉ: ______________________________

የትውልድ ቀን: ____________________ የተማሪውን የትምህርት መለያ ቁጥር: ______________

እባክዎን ከላይ ለተጠቀሰው ተማሪ ከሚከተሉት **<u>በአንድ አማራጭ ብቻ</u>** ምልክት ያድርጉ:

☐ **አማራጭ A**: ከላይ ስለተጠቀሰው ተማሪ ከላይ ያለውን የግል ማንነት መለያ መረጃዎችን እንዲለቀቅ ፈቃደኛ ነኝ።

ከምርጫ A በተጨማሪ ሌሎች ምርጫዎች ከተመረጡ፣ሌሎቹ ምርጫ(ዎች) ችላ ይባላሉ።ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ምርጫ A እንደመረጠ ያስባል።

**ወይም**

☐ **አማራጭ B:** ከላይ ስለተጠቀሰው ተማሪ ከላይ ያለውን የግል ማንነት መለያ መረጃዎችን ከወታደራዊ ክፍል በስተቀር እንዲለቀቅ ፈቃደኛ ነኝ፣ስለዚህ የተማሪ መረጃ ለውትድርና ክፍል ሊሰጥ አይችልም።

**ወይም**

☐ **አማራጭ C:** ከላይ ስለተጠቀሰው ተማሪ ከላይ ያለውን የግል ማንነት መለያ መረጃዎችን በህግ ካልተፈቀደ ወይም ከዚህ በታች ካለው የተለየ ፍቃድ ከሰጠሁት በስተቀር እንዲለቀቅ ፈቃደኛ አይደለሁም።

---

የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች ሊመረጡ የሚችሉት ከላይ ከተዘረዘሩት ሶስት አማራጮች ውስጥ አማራጭ Cን ከተመረጠ ብቻ ነው (ማለትም ፍቃድ ካልሰጡ)።ብዙ ልዩ ሁኔታዎች ሊመረጡ ይችላሉ።

ከታች ከተዘረዘሩት ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ በመምረጥ የግል ማንነት መለያ መረጃዎችን በተገለጸው መንገድ እንዲለቀቅ ተስማምተዋል።ከታች ያለውን ክፍል ካላሟሉ በስተቀር የልጅዎ መረጃ ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ አይካተትም።

☐ **የትምህርት ቤት ማውጫ እና የመማርያ ክፍል ስም ዝርዝር –** አዎ፣የተማሪዬን የግል ማንነት መለያ መረጃዎችን ለቤተሰቦቻችን፣ለሰራተኞቻችን እና ለPTSA እንዲገኝ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ።ይህ ስምምነት የትምህርት ቤቱ ጋዜጣ (የህትመት እና የዲጂታል ስሪቶች)፣የሽልማት ዝርዝሮች፣የምረቃ/የመጀመርያ መርሃ ግብር፣የቲያትር ማጫወቻ ሂሳብ፣የአትሌቲክስ ቡድን ዝርዝሮች/ፕሮግራሞች፣የባንድ/የሙዚቃ ፕሮግራም እና ሌሎች እውቅና ያላቸው ያካትታል።

☐ **ፎቶ/ቪዲዮ –** አዎ፣የተማሪዬን ፎቶግራፎች እና ቪዲዮዎች በትምህርት ቤቱ እና በዲስትሪክቱ ውጫዊ ድረ-ገጽ፣በማህበራዊ ሚዲያ እና በዲስትሪክት ህትመቶች ላይ እንዲለጠፉ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ።ይህ ስምምነት የክፍል ጋዜጣዎች እና በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ የኢሜይል ግንኙነቶችን ያካትታል።ስሞች <u>አይለጠፉም።</u>

☐ **የዓመታዊ መጽሐፍ/መማርያ ክፍል ፎቶ** - አዎ፣የተማሪዬ ፎቶግራፍ እና ስም በየዓመቱ መፅሄት እና የክፍል ፎቶ ውስጥ እንዲካተት ፈቃዴን ሰጥቻለሁ።

☐ **መረጃ ለOSPI ማጋራት –** አዎ፣የተማሪዬን የግል ማንነት መለያ መረጃ ለመንግስታዊ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSPI) ለማስተላለፍ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ እንዲሁም ይህንን መረጃ ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እድሎች ሲባል በስቴቱ ውስጥ ላሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሊተላለፍ ይችላል።

የፈራሚ ስም ______________________________ ቀን______________

የወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ የሆነ የተማሪ ፊርማ______________________________

*ይህ ቅጽ በተማሪዎ ትምህርት ቤት ይቀመጣል እና ምርጫዎችዎ በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ መረጃ ስርዓት ውስጥ ይመዘገባሉ።*

## ህዝባዊ መዝገብ(public record) ለመጠየቅ የማመልከት መብት ማስታወቂያ

**የዋሽንግተን ስቴት የህዝብ መዝገቦች ህግ(Washington State Public Records Act (RCW 42.56)** በስቴት እና በአካባቢ ኤጀንሲዎች የተያዙ ሁሉንም መዝገቦች፣ከተወሰኑ ሁኔታዎች ጋር፣ህዝባዊ መዳረሻን የሚጠይቅ የስቴት ህግ ነው።

በ RCW 28A.320.160 መሠረት፣የትምህርት ዲስትሪክቶች ወላጆች/አሳዳጊዎች በዋሽንግተን የህዝብ መዛግብት ህግ (RCW 42.56) መሰረት የትምህርት ቤቱን ሰራተኛ ዲሲፕሊን በተመለከተ የህዝብ መዝገቦችን የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።የህዝብ መዝገቦችን ጥያቄ ለሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለማቅረብ፣የፅሁፍ ጥያቄዎን ወደ: Office of the General Counsel: Attn: Public Records Request; SPS: MS 32-151; PO Box 34165: Seattle, WA 98124 ይላኩ።

ስለ የህዝባዊ መዝገቦች ህግ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን: https://mrsc.org/Home/Explore-Topics/Legal/Open-Government/Public-Records-Act/Public-Records-Act-Basics.aspx ይመልከቱ

---

የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች አቅም እና ቴክኖሎጂ ሳይገድበው የመስመር ላይ መረጃውን ለሁሉም ሰው ተደራሽ ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።የድር ተደራሽነት መመሪያዎችን እና ደረጃዎችን ማሟላት በቀጣይነት ለማሻሻል እየሰራን ያለነው ቀጣይ ሂደት ነው።

የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለተደራሽነት የተመቻቹ ሰነዶችን ብቻ ለመለጠፍ ቢጥሩም፣በአንዳንድ ሰነዶች ተፈጥሮ እና ውስብስብነት ምክንያት፣ተደራሽ የሆነ የሰነዱ ስሪት ላይገኝ ይችላል።በእነዚህ ውስን ሁኔታዎች፣ዲስትሪክቱ በእኩል ውጤታማ በሆነ አማራጭ ተደራሽነት ይሰጣል።